በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ እንተ ፡ ይሜግቡ ፡ ባቲ ፡ ወእንተ ፡ ይፈልጥዋ ፡ ወእንተ ፡ ይከልኡ ፡ ኪያሃ ፡ ወበእንተ ፡ ማኅደር ፡ ወናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ፈሊጠ ፡ አናቅጺሁ ፡ በክፍል ፡ ቀዳማዊ ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፫ቱ ።

በእንተ ፡ መብልዕ ፡ ወአልባስ ፡ ወማኅደር ፡ ወተግባረ ፡ እድ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመሢሓውያን ።

፳፻፪ ወመብልዕሰ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ መሢሓዊት ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ሕርመት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘከልኡ ፡ ሐዋርያት ፡ እምኔሁ ፡ በመጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ወበቀኖናቲሆሙ ፡ በብሂሎቶሙ ፡ ናሁ ፡ ሠምረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሠመርነ ፡ ንሕነኒ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢናንብር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ፆረ ፡ ክቡደ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ዘእንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ዘተኀድጉ ፡ ኪያሁ ፡ በግብር ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ትርኅቁ ፡ እምበሊዐ ፡ ደም ፡ ወሕንቅ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ አርዌ ።

፳፻፫ ወለእሉሂ ፡ የሐርምዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስቴቶሙ ፡ እምሕማም ፡ ነፍሳዊ ። እስመ ፡ ተሰናእዎ ፡ ምስለ ፡ መምለኪያነ ፡ ጣዖት ፡ በበሊዐ ፡ ዘይዘብሕዎ ፡ ለአማልክት ፡ ይከውን ፡ ዘይሳተፎሙ ፡ በአምልኮቶሙ ፡ ወይስሕቦ ፡ ዝንቱ ፡ ኀበ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖታት ። ወበእንተ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ እምሕማም ፡ ሥጋዊ ፡ ወነፍሳዊ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ታማስን ፡ ቲስሕተ ፡ ሥጋ ፡ ማስኖ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ሙስና ፡ ፍጥረት ፡ ወዓዲ ፡ ትወስድ ፡ ኀበ ፡ ሀጕለ ፡ አባል ።

፳፻፬ ወአኮ ፡ ዘአሕረምዋ ፡ እስመ ፡ ርኵስት ፡ ይእቲ ፡ በፍጥረታ ፡ እስመ ፡ እምፍጥረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይእቲ ። ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለነ ፡ በውስተ ኦሪት ፡ ዘይብል ፡ "ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡

በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ አምላክ ። ሁለተኛ ክፍል ። ስለ ፡ ምግባራት ፡ ለይተው ፡ ስለሚያስተዳድሩባትና ፡ እርሷንም ፡ ስለሚከለክሉባት ፡ ስለቤትም አሠራር፡ ይናገራል ። እነሆ ፡ አንቀጾችን ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ለይተን ፡ ተናግረናል ።

## አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

ስለ ፡ መብልና ፡ ስለ ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ቤትም ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ስለሚገባው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ።

፳፻፪ ሐዋርያት ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያትና ፡ በሲኖዶሳቸው ፡ በግድ ፡ ከምትተዉት ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ በላያችሁ ፡ እንዳናኖር ፡ እነሆ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቅዷል ፡ እኛም ፡ ደግሞ ፡ ፈቀድን ፡ ብለው ፡ ከከለከሉት ፡ በቀር ፡ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ የሚከለከል ፡ መብል የለም ። (የሐዋ ፡ ፲፭ ፡ ፳፯ - ፳፱) ። ይኸውም ፡ ደምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ አውሬ ፡ የነከሰውን ፡ ከመብላት ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፳፻፫ እኒህንም ፡ የሚከለክሏቸው ፡ በውስጣቸው ፡ ነፍስን ፡ (ሰውነትን) ፡ የሚጎዳ ፡ ሕማም ፡ ስላለ ፡ ነው ። ለጣዖታት ፡ የተሠዋውን ፡ በመብላት ፡ ጣዖትን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ በአምልኮታቸው ፡ አንድ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ይሆናልና ። ይህም ፡ ጣዖትን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ይስበዋል ። ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ የሚጎዳ ፡ ሕማም ፡ በውስጡ ፡ ስላለ ፡ ነው ። ይህች ፡ መፈጠርን ፡ ወደማጥፋት ፡ በሚያደርስ ፡ ጥፋት ፡ የሥጋን ፡ ባሕርያት ፡ ስምምነት ፡ ታጠፋለችና ። ዳግመኛም ፡ አካልን ፡ ወደማጕደል ፡ ታደርሳለች ።

፳፻፬ በተፈጥሮዋ ፡ የረከሰች ፡ ናት ፡ ብለው ፡ የከለከሏት ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ወገን ፡ ናትና ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡

ኵሎ ፡ ዘፈጠረ ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ” ። ወበወንጌልኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሰብእ ፡ ዘይክል ፡ አርኵሶቶ ። ወአፈ ፡ ወርቅኒ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብጠለ ፡ በዝንቱ ፡ ቃል ፡ መብዝኀታ ፡ ለትእዛዘ ፡ አሪት ።

፫፻፭ ወያጸንዕ ፡ ዘንተ ፡ ምክረ ፡ ዘተነግረ ፡ በአብረክሲስ ፡ ወውእቱ ፡ ቃለ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘይቤ ፡ ወዐርገ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልዕልተ ፡ ናሕስ ፡ ጊዜ ፡ ፮ቱ ፡ ሰዓት ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ወነዋ ፡ ርኅበ፡ ወይፈቅድ ፡ ይብላዕ ፡ ወእንዘ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ሎቱ ፡ መጽአ ፡ ድንጋፄ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወርእየ ፡ ሰማየ ፡ ርኅወ ፡ ወናሁ ፡ ሞጣሕት ፡ ዘእኑግዘ ፡ በ፬ቱ ፡ ጽንፈሁ ፡ አምሳለ ፡ ልብስ ፡ ዐቢይ ፡ እንዘ ፡ ይወርድ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ወሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ዘ፬ቱ ፡ እገሪሁ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይብል ፡ ተንሥእ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሕርድ ፡ ወብላዕ ። ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ እግዚእየ ፡ እስመ ፡ ኢበላዕኩ ፡ አነ ፡ ግሙራ ፡ ርኩሰ ፡ ወኢያድነሰ ። ወዳግመ ፡ ጸውዖ ፡ ወይቤሎ ፡ “ዘእግዚአብሔር፡ አንጽሖ ፡ ኢታስተራኵሶ ፡ አንተ ፡ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ” ።

፫፻፮ ወቅዱሳንኒ ፡ መምህራን ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ወካልአኒሁ ፡ አበው ፡ ለበዉ ፡ እምዝንቱ ፡ ከመ ፡ መፍቅድ ፡ ኮነ ፡ በቱ ፡ ፪ቱ ፡ ምግባራት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘንቡእ ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢነሐሲ ፡ እምዮእዜ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ኢአምኑ ፡ ዓዲሆሙ ፡ ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ ዘኢይደልዎሙ ፡ ለምእመናን ፡ ተራክቦ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ፍትሐ ፡ ብሊት ። ወካልእኒ ፡ ክሡት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኒሐሲ ፡ ከመ ፡ ኵሎሙ፡ እንስሳት ፡ ንጹሓን ፡ እሙንቱ ፡ ወኢንትከላእ ፡ እምተሲስዮ ፡ ዘይደሉ ፡ እምልባዌ ፡ ጠባይዕ ፡ ወሲሳይኒ ፡ ቦሙ ፡ ሀሎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሊዐ ፡ ደም ፡ ወሕንቅ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ አርዌ ።

፫፻፯ ወብዉሕ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ኢንትከላእ ፡ እምነ ፡

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

አየ ፡ የሚል ፡ እነሆ ፡ በኦሪት ፡ ተጽፏልና ። (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፰) ። በወንጌልም ፡ ወደሰው ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ሊያረክሰው ፡ የሚችል ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ተናግሮአል ። (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፩) ። አፈ ፡ ወርቅም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ከኦሪት ፡ ትእዛዝ ፡ ብዙዉን ፡ አሳለፈ ፡ ብሏል ።

፫፻፭ ይህንንም ፡ ቃል ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ የተነገረው ፡ ያጸናዋል ። ይኸውም ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነው ። ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊጸልይ ፡ ከሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጣ ። ያንጊዜ ፡ ተርቦ ፡ ሊበላ ፡ ሽቶ ፡ ነበር ። ምግቡንም ፡ እስኪያዘጋጁለት ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ መጣበት ። ሰማይ ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ። በታላቅ ፡ ልብስ ፡ አምሳል ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ የተያዘ ፡ መጋረጃ ፡ ወደምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ። በውስጡ ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ እንስሳ ፡ በምድር ፡ የሚንቀሳቀስም ፡ ሁሉ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ አሉ ። ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ተነሥ ፡ እረድና ፡ ብላ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ። ጴጥሮስም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ የረከሰ ፡ ምግብ ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅምና ፡ ልበላ ፡ አይገባኝም ፡ አለው ። ዳግመኛም ፡ ጠርቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ፡ አለው ። ይህም ፡ ቃል ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ። (የሐዋ ፡ ፲ ፡ ፱ - ፲፪) ።

፫፻፮ ቅዱሳን ፡ መምህራን ፡ አፈ ፡ ወርቅና ፡ ሌሎችም አባቶች ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ እንዳሉበት ፡ ተረዱ ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ስዉር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ገና ፡ ያላመኑ ፡ አሕዛብ ፡ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ እንደታዘዘው ፡ ምእመናን ፡ ሊገናኙዋቸው ፡ የማይገባቸው ፡ ርኩሳን ፡ እንደሆኑ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንዳናስብ ፡ ነው ። (ዘሌዋ ፡ ፲፫ ፡ ፩ - ፴ ። ፳፪ ፡ ፳፫-፯) ። ሁለተኛው ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ያለን ፡ ከመሆናችን ፡ የተነሣ ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሓን ፡ እንደሆኑ ፡ ሀውቀን ፡ የሚገባውን ፡ ከመመገብ ፡ እንዳንከለክል ፡ ነው ። ደምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ከአውሬ ፡ የተረፈውን ፡ ከመብላት ፡ በቀር ፡ ምግብነት ፡ እነርሱ ፡ አላቸው ።

፫፻፯ አእምሮን ፡ ወደማጥፋት ፡ ባሕርዩን ፡ ወደማናወጽ ፡ አካልን ፡ ወደማጉደል ፡ የሚያደርስ

አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

ኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአሕረሞ ፡ ፍትሐ ፡ ሕግ ፡ በእንተ ፡ ከዊኖቱ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ሙስና ፡ ሕሊና ፡ ወአማስኖ ፡ ጠባይዕ ፡ ወሙስና ፡ ሥጋ ። ወዝንቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይሜኒ፡ ለሲሳይ ፡ ወኢለመድኀኒት ፡ አኮ ፡ እምነ ፡ እንስሳ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ እምነ ፡ በቍላትኒ ፡ ካዕበ። ወዝንቱ ፡ ዘከመ ፡ እንስሳት ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሕምዝ ፡ ወዘከመ ፡ አራዊት ፡ መሣጥያን ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ዕፍራት ፡ ወመጕረጽ ። ወእለ ፡ ይሴስዩ ፡ ሕምዛተ ፡ ወበቍላተኒ ፡ ቀተልያን ፡ እለ ፡ ያማስንዎ ፡ ለልብ ፡ ወለኵሉ ፡ ሥጋ ፡ በበሊዖቱ። ወላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ እመ ፡ ተረክበ ፡ እምነ ዝንቱ ፡ ክፍል ፡ ፩ዱ ፡ ፆታ ፡ ዘያማስን ፡ ጥዑየ ፡ ወይፌውስ ፡ ድዉየ ፡ ይትገነሥ ፡ ጥዑይ ፡ እም በሊዖቱ ፡ ወለድዉይሰ ፡ ብውሕ ፡ ከመ ፡ ይብላዕ ፡ እመንገለ ፡ ፆታ ፡ መድኀኒት ። ወዳግማዊኒ ክፍል ፡ ዘይናፍቅ ፡ በመብልዕ ፡ አው ፡ ዘያናፍቅ ቢጾ ፡ ለእመ ፡ በልዐ ፡ ኪያሁ ።

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

ስለሆነ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከከለከለው ፡ በቀር ፡ ከምግብ ፡ ሁሉ ፡ እንዳንከለክል ፡ መሆን ፡ ይገባናል ። (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፩ - ፵፯) ። ይህም ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ለምግብነትና ፡ ለመድኃኒት ፡ ስለማይጠቅም ፡ ነው ። መከልከላችንም ፡ ከእንስሳት ፡ ብቻ ፡ አይደለም እንዲሁም ፡ ከአትክልትም ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይኸውም ፡ መርዝ ፡ ያላቸውን ፡ እንስሳት ፡ የሚነጣጥቁ ፡ አራዊትን ፡ ጥፍርና ፡ መውጊያ ፡ ያላቸውንና ፡ መርዞችን ፡ የሚመገቡ ፡ አራዊትን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ከመብላት ፡ ከአትክልትም ፡ ወገን ፡ ቢበሏቸው ፡ አእምሮ ፡ የሚያጠፉትን ፡ አካል ፡ የሚያጎድሉትን ፡ ከመብላት ፡ እንድንከለክል ፡ ነው ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ (ፍርድ) አትብሉ ፡ ከተባለው ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ምግብ ፡ ጤነኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚጎዳ ፡ በሽተኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚፈውስ ፡ ቢሆን ፡ ጤነኛው ፡ እርሱን ፡ ከመብላት ፡ ይከልከል ። በሽተኛው ፡ ግን ፡ የሚያድነው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሊበላ ፡ ይገባዋል ። ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ እየተጠራጠረ ፡ የሚበላውን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ በልቶ ፡ ሌላውን ፡ እንዲጠራጠር ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ይናገራል ።

፰፻፰ ወለእሉ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ አመረ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ በብሂሎቱ ፡ ውስተ ፡ መልእክተ ፡ ሮሜ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ። ወለዘኮነ ፡ ድኩመ ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንዕዎ ፡ ወኢትኩኑ ፡ ኑፉቃነ ፡ በልብክሙ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትአመን ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ብውሕ ፡ ለበሊዕ ፡ ይብላዕ ፡ ኵሎ ። ወድኩምሰ ፡ በፈቃዳቲሁ ፡ ይሴሰይ ፡ ሐምለ ፡ ወኢይመንኖ ፡ ዘይበልዕ ፡ ኵሎ ፡ ለዘኢይበልዕ ። ወኢይኰንኖ ፡ ዘኢይበልዕ ፡ ለዘይበልዕ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነቢሁ ። ወናሁ ፡ ተዐውቀ ፡ ወአነ ፡ እትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ርኩስ ፡ በኀቤሁ ምንትኒ ። ወባሕቱ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይትሔዘብ ፡ ከመ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ይከውን ፡ ርኩሰ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ወባሕቱ ፡ እኩይ ፡ ለብእሲ ፡ ሶበ ፡ በልዐ ፡ በዕቅፍት ። እመሰ ፡ ኢሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ኢንብላዕ ፡ ሥጋ ፡ ወኢንስተይ ፡ ወይነ ፡ ወኢናምጽእ ፡ ግብረ ፡ ካልእ ፡ ዘይትዓ

፰፻፰ ለእነዚህ ፡ ለሁለቱ ፡ ክፍሎችም ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ መልእክቱ ፡ በ፲፬ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ ። ሃይማኖቱ ፡ ደካማ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ቻሉት ። አጽናኑትም፡ በልባችሁም ፡ ተጠራጣሪዎች ፡ አትሁኑ ። ሁሉን ፡ ሊበሉት ፡ እንደሚገባ ፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡ ይብላ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እንደፈቃዱ ፡ ቅጠል ፡ ይብላ ። ሁሉን ፡ የሚበላው ፡ የማይበላውን ፡ አይንቀፈው ። የማይበላውም ፡ በሚበላው ፡ አይፍረድበት ። እግዚአብሔር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ እነሆ ፡ ታውቋልና ። እኔ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንም ፡ ርኩስ ፡ ምግብ ፡ እንደሌለ ፡ አምናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ርኩስ ፡ እንደሆነ ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ፡ ለእርሱ ፡ ብቻ ፡ ርኩስ ፡ ይሆንበታል ። ለሰው ፡ ክፉ ፡ የሚሆንበት ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ መብላቱ ፡ ነው ። እየተጠራጠሩ ፡ መብላት ፡ የሚጐዳ ፡ ከሆነስ ፡ ሥጋ ፡ አንብላ ፡ ወይንም ፡ አን

ቀፉ ፡ ቦቱ ፡ አኃዊነ ። ወዘሰ ፡ ናፈቀ ፡ ለእመ ፡
በልዐ ፡ ይትኴነን ፡ እስመ ፡ ኢገብረ ፡ ዘንተ ፡
በሃይማኖት ። ወኵሉ ፡ ዘኢኮነ ፡ በሃይማኖት ፡
ኃጢአት ፡ ውእቱ ።

፰፻፱ ወንሕነ ፡ አ ፡ ጉባኤ ፡ ጽኑዓን ፡ ይደልወነ ፡
ከመ ፡ ንፁር ፡ ድካመ ፡ ድኩማን ። ወበብሂ
ሎቱ ፡ ካዕበ ፡ ውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡
ለሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘ፮ቱ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡
ብውሕ ፡ ሊተ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢመፍትው ፡ ከመ ፡
እረሲ ፡ ለመኑሂ ፡ ሥልጣነ ፡ በላዕሌየ ፡ እስመ ፡
መብልዕ ፡ ንቡር ፡ ለከርሥ ፡ ወከርሥኒ ፡ ንቡር ፡
ለመብልዕ ። ዘ፱ቱ ፡ ወበእንተ ፡ በሊዐ ፡ ዘይዘ
ብሑ ፡ ለአማልክት ፡ ንሕነ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡
ጣዖት ፡ ኢኮነ ፡ ምንተኒ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡
ዓለም ። ወከመ ፡ አልቦ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበለ ፡
፩ዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕቱ ፡ ወባሕቱ ፡
አእምሮተ ፡ ግብርሰ ፡ ኢሀለወት ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡
ሰብእ ፡ ወመብልዕኒ ፡ ኢያቀርበነ ፡ ኀበ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ዘበላዕነ ፡
ንሕነ ፡ ዘንትዌሰክ ፡ ወኢበእንተ ፡ ዘኢበላዕነ ፡
አኮ ፡ ዘንሐጽጽ ። ዑቁ ፡ ነጽሩ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡
ሥልጣንክሙ ፡ ዕቅፍተ ፡ ለድኩማን ። ወከ
ማሁ ፡ እመሰ ፡ ኮነ ፡ መብልዕ ፡ ያስሕት ፡
እኁየ ፡ ኢይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ለዝሉፉ ፡ ከመ ፡ ኢያ
ስሕት ፡ እኁየ ። ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወናሁ ፡ ይደሉ ፡
ሊተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይ
በቍዓኒ ፡ ወኵሉ ፡ ምግባር ፡ ብውሕ ፡ ሊተ ፡
ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘያሤኒ ፡ ወየሐ
ንጽ ። ወኵሎ ፡ ዘይሠይጡ ፡ በምሥያጥ ፡
ብልዑ ፡ ወኢትሕትቱ ፡ በእንተ ፡ ሕሊናሁ ፡
ለዝንቱ ፡ እስመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡
በምልኣ ። ወእመቦ ፡ ዘጸውዐክሙ ፡ ፩ዱሂ ፡ እም
እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወፈቀድክሙ ፡ ከመ ፡ ትሖሩ ፡
ብልዑ ፡ እምኵሉ ፡ ዘአቅረቡ ፡ ለክሙ ፡ ዘእን
በለ ፡ ትሕትቱ ። ወእመሰ ፡ ይቤለክሙ ፡ ዝንቱ ፡
ዝቡሕ ፡ ለአማልክት ፡ ኢትብልዑ ፡ በእንተ ፡
ቃለ ፡ ዝኩ ፡ ዘይቤለክሙ ። ወብሂሎቱኒ ፡ ለጢ
ሞቴዎስ ፡ ዘ፬ቱ ፡ ወይትናገሩ ፡ በሕሡም ፡ ወየ
ሐርሙ ፡ መባልዕተ ፡ ዘፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለበቍዔት ፡ ወለአኰቴት ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡
ወየአምሩ ፡ ጽድቀ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈጠረ ፡



ጠጣ ። ወንድሞቻችን ፡ የሚጠራጠሩበትንም ፡
ሌላ ፡ ሥራ ፡ አናምጣ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡
እየተጠራጠረ ፡ ቢበላ ፡ ይፈረድበታል ። ይህን ፡
አምኖ ፡ አላደረገውምና ። በሃይማኖት ፡ ያልተ
ደረገ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። ( ሮሜ ፡
፲፬ ፡ ፩ - ፳፫ ) ።

፰፻፱ በሃይማኖት ፡ ጽንተን ፡ የምንኖር ፡ እኛም ፡ የተ
ጠራጣሪዎችን ፡ ደካማነት ፡ ልንታገሥ ፡ ይገባ
ናል ። ዳግመኛም ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በላ
ከው ፡ በመጀመሪያው ፡ መልእክቱ ፡ በ፮ኛው ፡
ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡
ይገባኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡
እንዲሰለጥንብኝ ፡ አላደርግም ። መብል ፡
ለሆድ ፡ ሆድም ፡ ለመብል ፡ ዝግጁ ፡ ነው ።
( ፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ) ። በዘጠንኛውም ፡ ክፍል ፡
እንዲህ ፡ አለ ። ለጣዖታት ፡ የተሠዋውንም ፡
ስለመብላት ፡ ጣዖት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡
እንዳይደለ ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ። ከአንድ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ እን
ደሌለ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡
ማወቅ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የለችም ።
መብል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያቀርበንም ።
እኛ ፡ ስለበላን ፡ የሚጨመርልን ፡ ስላልበላንም ፡
የሚጐድልብን ፡ የለምና ። ሥልጣናችሁ ፡ ( ፍላ
ጐታችሁ ) ፡ ለተጠራጣሪዎች ፡ እንቅፋት ፡ እን
ዳይሆን ፡ ሰወቁ ፡ ተጠንቀቁ ። እንደዚሁም ፡
መብል ፡ ወንድሜን ፡ የሚያስት ፡ ከሆነ ፡ ወን
ድሜን ፡ እንዳላስት ፡ ሥጋ ፡ ለዘወትር ፡ አል
በላም ። ( ፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፩ - ፲፫ ) ። በ፳፪ኛውም ፡
ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡
ይገባኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅመኝ ፡
አይደለም ። ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ የተገባ ፡
ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚበጅ ፡
የሚጠቅም ፡ አይደለም ። በገበያ ፡ የሚሸጡትን ፡
ሁሉ ፡ ብሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ተጠራ
ጣሪነት ፡ አትመራመሩ ። ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእ
ግዚአብሔር ፡ ናትና ። ካላመኑት ፡ ወገን ፡ የጠ
ራችሁ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ልትሄዱም ፡
ብትወዱ ፡ ሳትመራመሩ ፡ ያቀረቡላችሁን ፡
ሁሉ ፡ ብሉ ። ይህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ነው ፡
ቢላችሁ ፡ ግን ፡ ስለነገራችሁ ፡ አትብሉ ። ( ፩ኛ ፡
ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፫ - ፳፱ ) ። ለጢሞቴዎስም ፡ በጻፈው
በ፬ኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። ለሚያም

እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ምንትኒ ፡ ምኑን ፡ ሶበ ፡ ተወክፍዎ ፡ በአኰቴት ፡ ወኵሉ ፡ ይትቄደስ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበጸሎት ።



ኑና ፡ ጽድቅን ፡ ለሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ለጥቅምና ፡ ለምስጋና ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸውን ፡ ምግቦች ፡ እየተዉ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ይናገራሉ ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ከተመገቡት ፡ ርኵሰት ፡ የሌለበት ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ። ሁሉም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ በጸሎት ፡ ይቀደሳል ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፫ - ፭) ።

፫፻፲ በስ ፡ ፶ወ፪ቱ ፡ ወኢ.ያርኮስ ፡ ቀሲስ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ መባልዕት ፡ ኵሎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ዘየሐርምዎ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ። ወይደልዎሙ ፡ ለመሚሐውያን ፡ ወለካህናት ፡ እለ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለመነኰሳት ፡ ከመ ፡ ኢይጸመዱ ፡ ለዝንቱ ፡ ለብዝኀ ፡ ጾታ ፡ መባልዕት ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ወኢትፍግዕት ፡ በጣዕሙ ፡ ወሤናሁ ፡ ወልምላሜሁ ፡ ወኀብሩ ፡ ዘያጌጊ ። አላ ፡ ይሴሰዩ ፡ ለበቍዔት ፡ በዘይቀውም ፡ ሥጋ ፡ ኀዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ወዘተረክበ ፡ ለብዙኃን ፡ በመካናቲሆሙ ፡ ወዘመናቲሆሙ ። ወእግዚእነሂ ፡ ይቤ ፡ ምንትኑ ፡ ተደልዎ ፡ ወአስተሐምሞ ፡ በግብር ፡ ብዙኅ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ። ወዘይትፈቀድሰ ፡ ኀቤሁ ፡ ኀዳጥ ፡ ውእቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ውእቱ ። ወሐዋርያሁኒ ፡ ተለዎ ፡ ወይቤ ፡ አከለነ ፡ እምከመ ፡ ረከብነ ፡ ሲሳየነ ፡ ወዓራዘነ ። ወእግዚእነሂ ፡ ካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተዓቀቡ ፡ እምጸጋብ ፡ ወስካር ፡ ወወሀበ ፡ ብፅዓነ ፡ ለርኁባን ፡ ወለፅሙአን ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወረሰየ ፡ እሤቶሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፫፻፲ በስ ፡ ፶፪ ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ከሚከለክሉት ፡ በቀር ፡ ቄሱ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ከመባልዕት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውንም ፡ መብል ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ አይበል ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለሚሆኑ ፡ ለምእመናንና ፡ ለካህናቱ ፡ ይልቁንም ፡ ለመነኰሳት ፡ ዓይነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሚሆን ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ተገዢዎች ፡ እንዳይሆኑ ፡ ይገባቸዋል ። በጣዕሙ ፡ በመዓዛው ፡ በአለሳለሱ ፡ በሚያስት ፡ መልኩ ፡ እንዳይደሰቱ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። ሥጋ ፡ ለጥቂት ፡ ወራት ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ ለሚበቃ ፡ ያህል ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ለብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በዘመናቸውና ፡ በቦታቸው ፡ የተገኘውን ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ጌታችንም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለብዙ ሥራ ፡ መዘጋጀትና ፡ መጨነቅ ፡ ምንድን ፡ ነው ? ለእርሱስ ፡ የሚያሻው ፡ ጥቂት ፡ ነው ። ያውም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፮ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፴፩-፴፪) ። ሐዋርያውም ፡ ምግባችንና ፡ ልብሳችንን ፡ ካገኘን ፡ ይበቃናል ፡ በማለቱ ፡ መሰለው ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፰) ። ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ከስካርና ፡ ከጥጋብ ፡ ተጠበቁ ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፴፰ -፵) ። ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ ለሚራቡና ፡ ለሚጠሙ ፡ ብፅዕናን ፡ ሰጠ ። ዋጋቸውንም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አደረገ ። (ማቴ ፡ ፩ ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፩) ።

፫፻፲፩ ወበእንተ ፡ አልባስኒ ፡ ናሁ ፡ ተነግረ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በበገጹ ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሆሙ ፡ ወከልአ ፡ እምቀጠንት ፡ ዘያሠረግውዎሙ ፡ በኀብራት ፡ ዘገለፉ ፡ ቦሙ ፡ ወከመ ፡ ይኩን ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ልብስ ፡ ፀዓዳ ፡ ድልው ። ወከመሂ ፡ ኢይልበሳ ፡ አንስት ፡ አልባሰ ፡ እደው ፡ ወእደውኒ ፡ አልባሰ ፡ አንስት ፡ ወኢይደዩ ፡ እደው ፡ ሕልቀታተ ፡ ውስተ ፡ አፃብዒሆሙ ፡ ወኢአንስት ፡ ከመ ፡ ኢይልበሳ ፡ ወርቀ ፡ ዘተገብረ ፡ በልብስ ፡ ዘያስተሜክሕ ።

፫፻፲፩ ስለልብሶችም ፡ በየይነቱ ፡ እነሆ ፡ ተነገረ ። በቀለም ፡ ያስጌጧቸውን ፡ ልብሶች ፡ ከመልበስ ፡ ከለከለ ። ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ ማገልገያ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ ልብስ ፡ ወንዶችም ፡ የሴቶችን ፡ ልብስ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ወንዶች ፡ በጣቶቻቸው ፡ የምንዝር ፡ ጌጥ ፡ ቀለበት ፡ እንዳያደርጉ ፡ ሴቶችም ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ የሚያስመካ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ከለከለ ።